# የኢህአደግ በጥልቀት መታደስ ውጤቱ በጥልቀተ መታፈን ነው የመጣልንና እያመጣልን ያለው !!!!

ኢህአደግ በስብሰናል ሙሱና ኪራይ ሰብሳቢነት ወርሶናል መታደስ አለብን ፣ የአቅም ማነስና በስልጣን መባለግ ስለነገሰ ውስጣችን ጠርተን ስልጣናችንም ለተማረ ወጣት ትውልድ እንተካለን ብሎ በሁሉም ሚዲያዎች ፣በዲፕሎማሲ ፣በካድሬዎች መንደር ለመንደር
እች አገር ከኗጧት እንሆ 15 አመት አስቆጥረዋል ።

በ 15 አመታት ጉዘው ይቅር ሊታደሱ ፣ለወጣት ትውልድ ሊተኩስ ይቅር በአንጻሩ ሙሱና ፣ኪራይ ሰበሳቢት ፣ስልጣን እንደ ርስተ ጉልት ለብቻቸው ወደ ጎንና በርዝመት (በጥልቀት ) አሰፋፍተው በመያዝ ፣ሁሉም እናስወግደው አለን ብለው ቃል የገቡት በመካድ የሀገራችን ሀብት የአቤታዊ ፓርቲ ቻይና ሌጋሲ በመከተል በግል ባለስልጣናትና በገዥ ፓርት ስር ወደቀች ። ሀብቱ ተቆጣጠሩት ፣ባለጉበት እባለጉበትም ይገኛሉ ። በአሁኑ ጊዜ 20 (30) ሚሊየን ብር ወይ በደርዘን መኪና መግዛት ፣3/4/5 ህንጻ መስራት በኡንሽራንስ ፣በባንክ እጅግ ቡዙ ገንዘብ መካበት ፣ እያአንዳነዱ በለስልጣንና ቤተሰቡ አወቶማቲክ ካዝና ገዝቶ በንክ የማያውቀው ሀብት ገንዘብ ደብቆ ማስቀመጥ ወንጀል አይደለም ።ፍጹም ፍታቢሄር ነው ።
የዚሁ ተግባራቸው ለማስረጃነት ያህል በ 9 /3 /2009 ዓ ም በዝርዝር እንደአስቀመጥኩት ህዝባችን ከ 13 አመት እድሜ እስከ 45 አመትያለው ማለት ከጠቅላላ ህዝባችን ከ 65% እስከ 75% የሚሆነው ወጣት ጡንቻው አሳርፎ ሰርቶ የሚበላበት አጥቶ በሁሉም የሀገራችን ጠረፎች ወደሰደት እየተበታተነ ፣የኛ መሪዎች ግን ከላይ እንደጠቀስኩት ከቀበሌ እስከ ቤተ መንግስት ያለው መዋቅር ሀብታችን ተቆጣጥረው አሰፋፍተው ይዘው ፣በአሁኑ ጊዜ ሀብቱም በእጃቸው ፣ወታደራዊ ሀይልና ድህንነቱ ፣ዳኝነቱ በእጃቸው ይዘው ማናባቱ እኛን ይገፉናል እያሉን ይገኛሉ ።

የድህነቱ ጉዳይ ጠ / ም / ሀይለማርያም ደሳለይ በ 10 / 3 /2009 ዓ ም አዲስ አበባ ለሚገኙ ዲፕሎሚት ሰብስበው አስረግጠው እንደ ተናገሩተ ከ 100 ሚሊዮን ህዝባችን 50% ስራ አጥ ነው በተለይ ደግሞ እድሚያቸው ከ 15 አመት እስከ 35 አመት የሆኑ 8 ኛ/10 ኛ /12 ኛ / ክፍል የወደቁ ዩንቨርሲቲ የጨረሱ ወጣቶች 29 ሚሊዮን እንዳሉ አምነዋል ።ይህ የገጠር አርሶ አደር ብዛ ስራ አጢው አይጨምርም ። ጨምረው ደግሞ ሀገራችን በዚሁ 2009 ዓ ም እድገታችን ከነበረው ወደ 12 %እድገት ሊያሳይ ነው ብለውናል ።

በሌላ በኩል የሌሎች ክልሎችና አጋሮቻቸው በጥልቀት መታደስ የሚለው እንተውና ፣ በዚሁ በሰሜኑና መካከለኛ ክፍለሀገራችን የሚገኙ አንጋፋ አባታውያን ወይ ከኛ ወዲያ ማናባቱ ፣ያልናችሁ ካልፈጸማችሁ አትኖራትም የሚሉ በትእቢት የተወጠሩ የህወሐትና የበአዴን የማእከላይ ከሚቴ ስራ አስፈጻሚ ፣መነጋ ካድሬዎች ህዘቡን እንደጥገኛ ፓራሳይት ያመነመኑ ካድሪዎች ወይ ከፍተኛና መካከለኛ አማራር የሚባሉ ፣የ 2008 ዓ ም ስብሰባና ለስብሰባ የወጣ ገንዘብና ቁሳቁስ ሳንቆጥር ፣ እኖሆ ዘንድሮ ከመስከረም 7 /3 /2009 ዓም እስከአሁን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ፍጡራን ማእከላይ ከሚቴና ስራ አስፈጻሚ ከአምስት ጊዜ በላይ ፣ከከፍተኛና መከከለኛ አመራር አራት ጊዜ ከፊተኛ አበልና በወድ ሆቴል በፕላኔት ሆቴልና አከሱም ሆቴል ሌሎች ወድ ሆቴሎች እየበሉና እየተኙ ፣እንዲሁም በባህርዳር ፣በጎንደር ፣በወሉ ከፍተኛ ሆቴሎች ቢዚ ሆነውከ 90 ቀናት በላይ ቆይተዋል ። በተጨማሪ የሁለቱ ክልል ህዝብ ቢያንስ 30 ሚሊዮን የሚሆን ነዋሪ ህዝብ በውሎ አበል በዚሁ በመኸር ወቅት ከፍተኛ ከንዘብተመድቦ በስብሰባ ሲናጥ ከርመዋል ።

በዚሁ በቡዙ ቢሊዮን ብር ወጭ ተደርጎለት ሲደረግ የከረመው ስብሰባ አዳራሾች ዘግተው በውሼት ሲናናጡ ከርመው በመጨረሻ ይዘውት የወጡ ድል ቢኖር እርስ በእርሳችን ተበልተን ፣ለዚሁ ሰው በላ ወጣት ነይ የሚል ሙሁር እጃች ከምንሰጥ ፣እንዳንገላለጥ ፣ተሸፋፍነንና ተሻሽተን እንውጣ ፣ በማለት ተማምለው ነው የወጡ ።
ይህ የሆነበት ምክንያት እነዚህ ፍጡራን ቆርጠውና ተቆራርጠው ለመማታት ከሞከሩ ከላይ እንደገለጽኩት ሁሉም በሙሱናና በክራይ ሰብሳቢነት ስለበሰበሱ ፣የሀገራችን ሀብት በስፋትና በጥልቀት ስለወረሩት መቿውን ተመችውም አብረው ስለሚጠፉበተጨማሪም አነሱ ብቻሳይሆኑ የሚመቱ ከነሱ ጋር ነው።

የተሳሰረ ወደ ጎንና ወደ ጥልቀት አንሰፋርቶ የሀገር ሀብት አብሮ የወረረ ዘመድ ልጅ ጓደኛ አብሮ ሊበላ በመሆኑ ሁለቱ በአባታውነት የተወቀሩ አንጋፋ ፓርቲዎች እጅግ ጥሩነን ምንም እንካን አንድአነድ ስህተቶች ቢኖሩም ለመለካም ስረችን የሚሸፈኑአይደሉም ብለው ወጡ ።
ከተሰብሳቢዎች ይናፈሱ ከከረሙ ለመጥቀስ ፣የሁለቱ አንጋፋና አባታውያን ፓርቲዎች አማራርና ታማኝ መዋቅራቸው ስልጣናችን ለዚሁ ሰው በላ ወጣት ትውልድ ካስረከብን ከነዘር መንዘራችን ሊበላንና ሊወረን ነው የሚል ስጋት እንዳላቸው ይናገራሉ ።
ሁለቱ አንጋፋ ፓርቲዎች ህወሐትና በአዴን የስልጣን ስግሽግ ያላደረጉበት ከስጋት የመነጨ መሆኑ ምንጮች አረጋግጣል ።
ሌላ ግን ለህዝቡ የስልጣን ሽግሽግ ወይ ሽምሽር አድርገናል ብለው ለህዝብ ለመታለል ወይ እነዚ ፉጡራን ሊያሻሽሉ ናቸው እንዴ

የሚል መንፈስ ለመፍጠር ፣ታማኝነትን ለማግኜትን ሲባል ፣ቡዙ ተሰሚነት የሌላቸው የቀበሌና የወረዳ ዝቅተኛ ስልጣን ያላቸው በተጨማሪም ባደረጉት ስብሰባ ወጣወጣ ብለው ሙሱናና ኪራይ ሰብሳቢነት የሚያጋለጡ የነበሩና ሲዳፈሩ የነበሩ እንደሚያባሩሩ ከወዲሁ ከውስጣቸው እየተናፈሱ ናቸው ።

በህወሐት ወስጥ ከኤፈርት ውጭ ከስራ አስፈጻሚ ጀምሮ እስከ ታችኛው የወረዳና የቀበሌ ባለስልጣናት ፣ልጆቻቸው ፣ዘመድ አዝማዳቸው በቡዙ ሚሊዮን ብር የዘረፉ ፣ ከሁለት በላይ ምንጩ የማይታወቅ ህንጻዎች የሰሩ የህዝብ መሬት እቀሙ የሸጡ ፣ለድሆች ተብሎ በእርዳታ የመጣ ገንዘብ በውኼት ፊርማ ሰርቀው ሚሊዮኖሮች የሆኑ መኪኖች የኮንስትራክሽ ማሽነሪ ወረው የገዙ ፣የእርሻና እንድስትሪ ባለሀብቶች የሆኑ ፣የገንዘብ ወለድ ወይ አራጣ የሚያሳማሩ በአጠቃላይ ዘርዘራቸው ሀብታም ያደረጉ እያሉ ። አቶ ስዩም መስፍን ግን በህወሀት ፓርቲያችን አንድ አንድ ጦለቆምቆም ( ከጠፍጠፍ ፣ትንሽ ትንሽ ) ማንሳት ቢኖርም የተጋነነ አይደለም በማለት አንደኛ በህወሐት መሪዎች ተወዳጅ የሆነች ውራይና መጽሄት ሁለተኛ በመድረኩ በሰነዘሩት ሀሳብ ህዝብን አግራሞት ፈፕረለታል ።

ሀቁ ግን በትግራይና በአማራ ክልል 26 አመት ሙሉ በመንግስትና እርዳታ ሰጭዎች የተመደበ ባጀት ከ 65 % በላይ ተመዝብሮ ለምቶ የሚባልም ጥራት የለውም ።ለዚሁም ለማስረጃነት የተሰሩ የስፋልት መንገድ ባጭር ጊዜ ፈራርሰዋል ፣የተከዜ አድሮ ፓዎር 75 % አይሰራም በአማራ ክልልም እደዚሁ ተባላሽቷል ሙሱናም እዛው የጎላነው ። በአጠቃላይ እነዚህ ፍጡራን የገቡት ቃል የካዱ ስለሀገርና ስለህዝብ እንስራ የሚል ቀና ሀሳብ የሌላቸው ከህዝብ ጥቅም የግላቸውና የዘር መንዝራቸው ብቻ የሚቆረቆሩ ሆነዋል ።

የህወሐትና የባአዴን አመራር በሁለቱ ህዝበ የፈጸሙት ምዝበራ መሱናና ኪራይሰብሳቢነት እንደይ ጋለጡ ታሳቢ በማድረግ በሁለቱ ህዘብ በትግራይና አማራ ፣በአማራና በቅማንት የዘር ግጭት ሆንብለው ፈጥረው በሞቶ የሚቆጠሩ ዜጎች የሞቱበት የዛ እጥፍ እጥፍ የቆሰሉበት ፣ሞቶ ሽዎች ሀብታቸው ተወርሰው የተፈናቀሉበት ፣በቢልዮን ብር የመንግስትና የህዝብ ሀብት የወደመበት ፣ቡዙ ህጻናት እርጉዝ አዛውን ካገራቸው የተፋናቀሉበት የሞቱበት በአማራሩ ተንኮልና ቅስቀሳ እያለ ፣የበአደን አማራር ደመቀመኮንንና ገዱ እንዳርጋቸው ተራ ማስጠንቀቅ ሰጠቶ ሲበተን ህወሀት ደግሞ እንዳንገላለጥ ብሎ ዝምታን መርጦ ወጣ ። በጎንደርና በጎጃም በትግራይ ህዝብና በቅማንት የደረሰ ግፍ ተጠያቂዎች የህወሐትና የበአዴን አመራር ጸሀይ የመታው ሀቅ እያለ ያለፍርድ መለቀቃቸው የፓርቲዎች ወደ ጸረ ህዝብ የወረዱ መሆናቸው ያሳያል።
ከአስገደ ገብረስላሴ መቀለ ፣

11 / 3 / 2009 ዓ ም